<u>PANORAMA # XX</u>

## <u>የትዝብት አድማስ</u>

### ሚያዚያ ሦስት 2000 ዓም

### <u>አሸባሪው ወያኔ እንጅ</u>
### <u>ታጋይ ሀገር ወዳድ ድርጅቶች አይደሉም</u>

የቃላት አፈታት፣ አፈረጃጀትና አጠቃቀም፣ በአመዛኙ እንደ የግለሰቡ፣ ዘመኑና ሁኔታው እየተተረጎመ ቆይቷል:: የአንዱ ሞት ለሌላው ሕይወቱ ይሆናል:: ለአንዱ ቆንጆ ለሌላው መልከ-ጥፉ እንደሚባለው ነው:: ስሜትና አይታ መለያያቱ አንዳለ ሆኖ ፣ የአንድ ነገር ዕውነተኛ ም ንነት ግን ሊለወጡት አይቻላቸውም:: ለአንዱ አርበኛ ለሌላው ሽብርተኛ፣ የአንዱ ሀቀኛ የሌላው ቀማኛ፣ ቀጣፊና አጭበርባሪ እየሆነ ሲፈረጅና ሲፈረድበት የኖረ ነው:: የትላንት ሀገር ገንጣዮች የዛሬ መሪዎች በሆኑበት ሀገር ደግሞ የነገሮችና የሁኔታዎች አተረጓጎም ቅጥ-አምባራቸው እየተበዋወዘ በመሄድ ላይ ይገኛል:: ምንም ጊዜም ቢሆን ሊበሏት የፈለጓትን አሞራ የዥግራ ስም እንደሚሰጧት ሁሉ ሊያገኙት ያልቻሉትን የወይን ፍሬ ደግሞ ሆምጣጣ ስለሆነ ተውኩት መባሉ የተለመደ ነው:: ተፈጥሮ በቅራኔዎች የተከበበች ነች ቢባልም፣ እና ደግሞም፣ ጨለማ በብርሀን ፣ መዓልት በሌሊት፣ ፀሀይ በዝናም፣ ክረምት በበጋ፣ ክፋት በደግነት፣ ጭካኔ በርኅራኄ፣ ፍርሃት በድፍረት፣ ውርደት በኩራት፣ ወዘተ ቢፈራረቁም ቅሉ፣ ለፖሊቲካም ሆነ ለኢኮኖሚ ጥቅም ሲባል የአንዱን ስም ለሌላው መስጠት፣ ስሙን የለወጡት ነገርና ሁኔታ በምንም ተዓምር በተፈጥሮ ያገኘውን ማንነት ምንነት ሊለውጡት አይችሉም:: የወያኔ የጎሳ ሽበርተኞች ከምኒልክ ግቢ ገብተው፣ የመነኮሴ ቆብ ቢደፉም፣ የበግ ለምድ ቢያጠልቁም በባኅሪያቸው በድርጊታቸው ከእኩይነት ከወንጀል ተግባራቸው ሊላቀቁ አልተቻላቸውም::

በጊዜ ብዛትም ሆነ በቦታ መለዋወጥ ምክንያት፣ ሰዎችና ሁኔታዎች በመሠረቱ ተፈጥሯዊ መለያቸውን ሊለውጡ የሚችሉ አይመስልም:: የወያኔ ግለሰቦች ሲፈጠሩ ጀምረው አብሮ አደግ ባኅርያቸውና ግብራቸው በምንሊክ ቤተመንግሥት ውስጥ ስለመሸጉ ብቻ ሊለውጡት ከቶ አልተቻላውም። አይቻላቸውምም:: ጫካ በነበሩበት ዘመን ሲፈፅሙት የነበረውን የአሸባሪነት ድርጊት፣ የምኒልክን ካባ ለመጎናፀፍ ቢከጅሉም ያቆሙታል ይለውጡታል ብሎ መጠበቅ የተፈጥሮን ሕግ መካድ ይሆናል:: “የመንግሥት” ሥልጣን በመያዙ ምክንያትም መንግሥታዊ ሽብርተኝነት ከመቀጠል ያገዳቸው የሕግም

ሆነ የሞራል ልጓም አለማግኘታቸው፣ ለዚህ አባባል ተጨማሪ ዋቢ የሚያስፈልገው አይደለም:: ከት ብሎ ሊያስቅ የሚችለው ግን፣ የአባዬን እከክ ለእማየ ልክክ መሆኑ ነው:: የኢትዮጵያን ብሔረ-ሰቦች እርስ በርስ እንዲጨፋጨፉ ለማድረግ የሞከሩትም፣ ከተፈጥሯቸው ባገኙት ባኅርይ ብቻ ሳይሆን፣ የዛሬ 17 ዓመት ሎንዶን ላይ የበላይ ጠባቂዎቻቸው፡ በአጎናፀፏቸው የዲፕሎማቲክ ሽብርተኝነት ውሳኔና ድጋፍ ጭምርም ነበር:: እነዚህ ኃይሎች፣ በማያገባቸውና በአልቸገራቸው በኢትዮጵያ ጉዳይ ጣልቃ በመግባት በአካሄዱት/ በተጠቀሙበት የዲፕሎማቲክ ሽብርተኝነት፣ ሀገራችንን በዘለቄታ መልኩ ሊጎዳት የሚችል ሽብር ፈጽመዋል:: በሽብራቸውም ሀገራችንን ማስገንጠል ብቻ ሳይሆን፣ በሽብርተኞች እንድትገዛ አስደርገዋል:: በሽብር የተወለደ፣ በሽብር ኖሮ፣ በሽብር እንደሚጠፉ ግን መጀመሪያወኑም አላሰቡበትም:: በደም የሚኖር በደም እንደሚጠፉ ሁሉ፣ በሽብር የሚኖሩም በራሳቸው ሽብር ይከስማሉ:: ሽብርተኛው ወያኔም ከዚህ ነፃ ሊሆን አይችልም:: ዛሬ ለዲሞክራሲ ሥርዓት በመታገል ሕዝባቸውን ከወያኔ የዘርኝነት ጭቆና ለማላቀቅ የሚታገሉት ሀገር ወዳድ የተቃዋሚ ድርጅቶች፣ ጉደኛው መለስ ዜናዊ አሸባሪዎች ብሎ ጠርቷቸዋል:: ከዚህ አልፎ ተርፎም፣ በስደት ሆኖ የሚቃወመውን ዜጋ ሁሉ፣ ሽብርተኛ ስለሆነ የመኖሪያ ፈቃድ አትስጡብኝ እያለ ደጅ በመጥናት ላይ ይገኛል:: ሊሳካለት ግን አልቻለም:: ይህ ሽብርተኛ የመለስ ቡድን፣ መንግሥታዊ ሽብርን እየተጠቀመ ንፁሃን ኢትዮጵያውንን እንዳልጨፈጨፈ ሁሉ፣ በሠላማዊ መንገድ የሚታገሉት ዜጎችና ድርጅቶችን በሽብርተኝነት ፈርጆ ለፍጀት እየተዘጋጀ ለመሆኑ ተደርሶበታል:: ይህንን መከላከል ደግሞ የሁሉም ዜጋ ተቀዳሚ የትግል አጀንዳ ሊሆን ይገባል::

መንግሥታዊ ሽብር ከሌሎች ሽብሮች ሁሉ በጣም የከፋና የከረፋ የሚሆነው፣ ሽብርተኝነቱ ሀገር ያወቀው ፀሀይ የሞቀው በመሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ሽብሩን ለማካሄድ፣ ማነኛውም ነገር ሁሉ በግልፅና በገፍ ስለሚያገኝም ጭምር ነው:: ፕሮፓጋንዳው፣ ገንዘቡ፣ የጦር መሳሪያው "የሕግ ምርኩዙ" ፣የዲፕሎማቲክ ሽፋኑ ወዘተ.. ሁሉ በእጁ- በደጁ ስለሆነለት፣ መንግሥታዊ ሽብር፣ ገደብ የለሽ ሽብር ማከናወኑ የወያኔ የጎዳጣንና ዘረኛ ሥርዓት ኅያው ምስክር ነው:: በመንግሥት ደረጃ ያለ ማንአለብኝነት፣ ሕዝብን በጅምላ ከመጨፍጨፍ የከፋስ ወንጀል ከየት ይመጣል? ወያኔ አሁን በያዘው ሥልጣን በመተማመን የሚያካሂደው መንግሥታዊ ሽብርተኝነትና ሽብር ካልተባለ፣ ሌላ ማን ሽብርተኛ ሊባል ይችላል? መንግሥታዊ ሽብርተኝነት ለመቋቋም በአልሞት ባይ ተጋዳይነት ዜጎች የዘር ማጥፋት ወንጀል በጅምላ ሲካሄድባቸው ብሎም በሕይወት ሊደርስላቸው የሚችል የሀገር ውስጥም ሆነ ዓለም አቀፍ የአስቸኳይ ገላጋይ ካለደረሰላቸው ሕይወታቸውን ለማዳን ሊኖራቸው የሚችለው ምርጫ ምን ይሆናል? አደጋውን ለማምለጥ ከሸሹበት-ከተሰደዱበት ሀገር ድረስ ነፍሰ-ገዳዮችን በመላክ ግድያ የሚፈጽምባቸው ወያኔ ሽብርተኛ ካልተባለ፣ ይህ ስም

ለማን ይሰጠው? ዛሬ በሀገራችን በስፋት እየተካሄደ ያለውን የወያኔ ሽብርተኝነትን ለመቋቋም፣ ዜጎች ሰላማዊ አመፅ እያደረጉ ባሉበት በአሁኑ ወቅት፣ ሰላማዊ ትግላቸውን የሽብርተኝነት ቀለም ለመቀባት ደፋ ቀና የሚለው ወያኔ ምን ያህል ዙሪያው ገደል እንደሆነበት ከማስረዳቱ በቀር ሌላ ትርጉም አይሰጠውም:: ሲዋኙ ዓይታ፣ አይጥ ሰመጠች ቆሪ ገብታ፣ እንደሚባለው፣ ከወያኔ በፊት የነበረው ደርግ ወያኔ ሽብርተኛ ነው ሲለው የነበረውን አባባል፤ ዛሬ እነ መለስ ዜናዊ የዘረኛ አገዛዛቸውን በመቃወም የሚታገለውን ሁሉ ሽብርተኛ ማለታቸው አያስደንቅም:: የመንግሥት ሥልጣን ጨበጥን ብለው ልባቸው ውልቅ ስለአለ፣ እነርሱም በተራቸው በሕዝባዊ አመፅ ድራሻቸው እስከሚጠፋ ድረስ የደርግን ኡኡታ ከመጻጨር ወደኋላ አይሉም:: በአሁኑ ወቅት፣ በነመለስ ዜናዊ ፕሮፓጋንዳ የሚነዛው ማስፈራሪያና ማስጠንቀቂያ፣ ልክ በደርግ ዘመን ሲደረግ ከነበረው ፕሮፓጋንዳ በይዘትም ይሁን በቋንቋ፣ በመጻጨርም ይሁን በሀኬት ተመሳሳይ መሆኑን ስንገነዘብ፣ ታሪክ በተለያየ አጋጣሚ እራሷን ትደግማለች የሚለውን አባባል ለመታዘብ በቅተናል::

ይህች ኢትዮጵያ የምትባለው ሀገራችን መቸም የተያዘ የተረዘዘው ገዥዋ ሁሉ፣ የሚፈራረቅባት እንዳሻው እየገዛ እየነዳ፣ ግፍ እየፈፀመባት መሆኑ በተደጋጋሚ የተገለፀ ነው:: የወያኔ መሪዎችም በአቅማቸው ይህንኑ ከመፈፀም አልተቆጠቡም:: ከሌሎቹ ቀደምት አምባገነኖች የሚለያቸው ብዙ መሠረታዊ ልዩነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ግን፤ ለኢትዮጵያ ያላቸው ጥላቻ ለሕዝቡም ያላቸው ፍርሃት የተን ያህል ስር የሰደደ መሆኑ ነው:: ያም ሆኖ አንድ መጤን ያለበት ነጥብ ግን፣ ይህ ስር የሰደደው የሕዝብ ጥላቻ፣ ወደ ሕዝብ ፍራቻ መዘዋወሩ ነው:: በጥላቻ ላይ የተመሠረተ ፍራቻ ደግሞ ምን ያኀል የጎሌና ዕረፍት እንደሚነሳ ጠልቶ ከሚፈራው ሰው የበለጠ የሚያውቀው የለም:: በአመዛኙ የወያኔ መሪዎች ዛሬ የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚፈሩት ከአላቸው ስር የሰደደ ጥላቻ የመነጨ ነው:: ከሰው ልጅ የሰውነት ክፍል በጣም አስቀያሚው፣ ዐባይ ከንፍሩ (ውሽታም ምላሱ) እንደሆነ ሁሉ፣ ከጥላቻ የመነጨ ፍራቻ ደግሞ የሚያመጣው ጭካኔ ይህ ነው አይባልም:: ተደጋግሞ በታሪክ እንደታየው ደግሞ፣ የመጨረሻዎቹ ፈሪዎች አምባገነኖች ናቸው:: በተፈጥሮ ያገኙት ኃሞት በጭካኔ ድርጊታቸው ተሟጥጦ ስለአለቀባቸው ድፍረት የሚባለው ጥረ-ነገር በሙሉ ተሰልቦባቸዋል:: ሀሞተ ቢሶች ብቻ ሳይሆኑ ፈሪዎችና ጨካኞችም ናቸው:: በመሆኑም በሥልጣን ጊዜያቸው ሁሉ ታዲያ የመኖር ሂደት፣ ሕዝብ እየጠሉ መግዛት፣ እየገዙ መፍራት፣ እየፈሩ መሸሽናነብ ነው:: የአምባገነኖች ፍርኃት በትክክል የተንፀባረቀው በመንግሥቱ ኃይለማርያም፣ በቬኒቶ ሙሶሊኒ፣ በኢዲ አሚን ወዘተ. ነው:: ሲኖሩ በሽብር፣ ሲገዙ በሽብር፣ ሲሸሹ በሽብር የአምባገኖች ባኀርይና ተግባር ነው:: በሽብር ተፈጥሮ፣ በጥላቻ ኖሮ፣ በፍርኃት መሸሽ በሽሽት መፈፀም የአምባገነኖች አልፋና ኦሜጋ ሕይወት ነው:: በታሪክ ቆሻሻ የሚወረወር የሀዘንና የሽብር ሕይወት!

በምክንያት የተደገፈ ክርክር ሲሟጠጥ፣ ውንብድና የሽብርተኝነት አካል ይሆናል። የሽብርተኝነት ብዛቱና ዓይነቱ የተለያየ ቢሆንም፣ መንግሥታዊ ሽብርተኝነት የመጀመሪያውን ደረጃ የያዘ አስፈሪና አውዳሚ ክስተት ነው። ወያኔና ደርግ በዚህ የተካኑ ናቸው። ኢትዮጵያ በውጭ ኃይሎች በተሰነዘረባት ጥቃት ምክንያት የዲፕሎማቲክ፣ የፕሬስ፣ የኢኮኖሚ ማዕቀብ፣ የቅኝ ግዛት የባኅል ሽብርተኝነት ሰለባ በመሆን ስትጎዳ ቆይታለች። አሁንም ከእነኝህ ሽብሮች ነፃ አልወጣችም። በመሆኑም የሽብርተኝነት ትርጉምና ስያሜ ለመስጠት ወያኔ ግብረ-አበሮቹ የሞራል የህግ የበላይነት አይኖራቸውም። ዲያብሎስ ስለመንፈስ ቅዱስ ለመስበክ ተፈጥሮው እንደማይፈቅድለት ሁሉ፣ ከወያኔ የግፍ አገዛዝ ለመላቀቅ የሚታገሉትን ዜጎች ሁሉ ወያኔና አለቆቹ፤ በሽብርተኝነት ሊፈረጁቸው የሚበቃቸው የሞራል ሥልጣን የላቸውም። ምን ጊዜም ቢሆን፣ ለሀገር ነፃነት የሚታገሉ፣ ለሕዝባቸው አርበኛ፣ ለገዥዎች ግን መጋኛ ናቸው። ምንም ምን ትርጉም ይሰጠው፣ ጭቆና እስካለ ድረስ ትግል ይኖራል፣ መታገል ካለም፣ መሥዋዕት መኖሩ አይቀሬ ነው። መሥዋዕት እየከፈሉ መታገል የሽብርተኝነት ስም ከአሰጠ ደግሞ ለወያኔ ደስ አለው አላለውም ይሁነለት ማለት ይገባል።

የመለስ ቡድን ዛሬ በኢትዮጵያ ከሥልጣን ተቆናጦ የሚገኘው በሕዝብ ፈላጎት ምርጫ ሳይሆን በጉልበት ነው። እንደ ሌሎች አምባገነኖች ሁሉ፣ መለስ ዜናዊ በጦሩ ይመካል። በአፋኞቹ ተቋሞቹ፤ በሰላዮቹ ነፍሰ ገዳዮቹ ይኩራራል። ማሌሊት በሚለው ስሪት በዙሪያው የሰበሰባቸው ካድሬዎች ዓይንና - ጆሮ ሆኖውልኛል ባይ ነው። በዙሪያው እበላ ባዮችንም ኮልኩሏል። ዋናው መመኪያው ግን የአጋዚ ነፍሰ ገዳይ ቡድንና የፌደራል አፋኝ ክፍል ናቸው። የእነዚህ ተቋማት አባላት እንዳያፈነግጡ ደግሞ በውስጣቸው ሰላዮች መንጣሪዎች ማሰማራቱ ብቻ ሳይሆን፣ ሊደለሉ የሚችሉትን በገንዘብ፣ በከተማ ቤትና ቦታ ወዘተ መሸንገያ ያንበረክካል። ጦሩ የሕዝብና የሀገር ሳይሆን፣ የድርጅት ነበር። ዛሬ ደግሞ የተባለው ድርጅት ፈራርሶ ጦሩ ታዛዥነቱ ለግብዙ መለስ ዜናዊ ሆኖ ተከስቷል። መለስ ዜናዊ ዛሬ በመላ ሀገሪቷ ላይ የበላይነቱን የሰየመው በጨፍጫፊው ጦር አማካኝነት ነው። ምርጫ ባለው ቧልት እንኳ ሳይቀር በአጋዚ ጦር ጭፍጭፋ እንደሚያካሂድ ባለፈው ግንቦት ወር 1995 ዓም በአዲስ አበባ በሌሎች ቦታዎች ያካሄደው ግድያ ምስክር ነው። በጋምቤላ የተካሄደው ፍጅት የዘግናኝ ምሳሌ ነው። ሰላማዊ ሰልፍ በኃይል በመበተን በመግደል፤ የተሰደዱትን ቤተሰቦች በማሰር በመግደል ያሰራቸውን ደብዛ በማጥፋት፤ ከሥራ በማባረር በማስፈራራት መለስ ዜናዊ የሚገዛው በኃይል ነው። ይህ ደግሞ በግሪኮች አፈ ታሪክ "ሁሌም ተንጠለጠለ" እንደተባለው የዴሞክራሲ ጎራዴ ሳይሆን፣ ነጋ ጠባ ንፁህ ዜጎችን በመጨፍጨፍና አንገታቸውንም እየቀነጠሰ በደም የሚያጨቀይ ሰይፍ ነው። ቀይ ቀለም የተሞሉ ጠርሙሶች በአደባባይ እየሰበረ የሺዎችን ደም አፈሳለሁ ያለው ባለዛሩ ኮለኔል ዛሬም በገቢር በባሰ ፈሪና ነፍሰ ገዳይ ቡድን ተተክቷል።

ሁለቱም ሥርዓቶች ታማኝነታቸው ለሁለት የተለያዩ ባዕዳን ጌቶቻቸው እየገለፁ የሀገራችንን የነጻነት ልዕልና አሳልፈው ሰጥተዋል:: ወያኔ፣ በየአደባባዩ በርከታ ሬሳ በየቀኑ በአደባባይ ባይሰጣም በአንድ ቆረጣ ምት ሺ አማራ፤ ሺ አኝዋክ፤ ከዚያ ያላነሰ ኦሮሞ፤ ሶማሌ ወዘተ በወያኔ ተመትሯል፤ ተጨፍጭፏል:: አልቋል:: ግድያው አሁንም እንደቀጠለ ነው:: ሽብር ወይም በኃይል ላይ መመካቱ የወያኔ አገዛዝ ድርጊት መግለጫው ነው:: ከደደቢት እሰከ አራት ኪሎ የተጓዘበት ሂደትና ጎዳና የደም ጎርፍና የሬሳ ክምር ፖለቲካ ነው:: ሽብር ሥርዓቱ ይገልጠዋል:: ሕዝብ ካላሸበረ በኃይሉ ካልተጠቀመ የመለስ አገዛዝ እስከዛሬም አይበረክትም ነበር:: ወደፊትም ቢሆን ከዚሁ የሽብር አገዛዝ ውጪ የመለስ መንጋ በሌላ መልክ ሊገዛ ይሞክራል ብሎ መጠበቅ ዘበት ነው:: የሚያሳዝነው ግን ባዕዳ የበላይ ጠባቂዎቹ ይህን ግፍና በደል እያዩ እየሰሙ በሥልጣን እንዲቆይ የሚያደርጉት ትብብር ነው:: ባይረዱት እንጅ ለእነርሱም የወደፊት ጥቅም፣ ከወያኔ ይልቅ የሰማኒያ ሚሊዮን የኢትዮጵያ ሕዝብ ወዳጅነት ይበልጥባቸው ነበር:: ኢትዮጵያንና ዜጎቿን መበደል ደግሞ የኋላ ኋላ ጦሱ ብዙ፣ ሰበቡ በርካታ ጥንቁ መራራ ነው::

ይህ እስከሆነ ድረስ ደግሞ በደልን በጫንቃው ላይ ተሸክሞ መኖር የሚሻ ማንም የለምና የኢትዮጵያ ሕዝብም የተሻለ ኑሮ ለመኖር፤ ከሽብር ተገላግሎ ሰላምንና ማህበራዊ መረጋጋትን ለማግኘት፤ አምባገነንነትን አስወግዶ በዴሞራሲያዊ ስርአት ውስጥ የወደፊት እድሉንና እጣውን ለመወሰን እንዲያስችለው ለውጥን ማምጣት ቀና ፍላጎቱ ነው። ይህን ለማግኘት ደግሞ፣ ይህ የዘረኞች ጥርቅም ከሥልጣን ለማባረር፤ የሽብሩ ሰለባ ላለመሆን መጣር አለበት ማለት ነው:: ይህም ከትግል ርቆ አንገትን ደፍቶ መገዛት ማለት አይደለም:: የአምባገነኖች ሽብር በቀይ ሽብሩ እንደታየው፣ ከበቀል ስሜትና ከግድያው ባሻገር ሊያጠቃ የሚፈልገው ቀሪውን በህይወት ያለውን ነው:: ይህንን መልዕክት ለቀሪው፣ ለቋሚው በማስተላለፍ ሀሞቱን ለማፍሰስና በህይወት እያለ የተሳቀቀ በድን ሊያደርጉት ይሞክራሉ:: ቀይ ሽብር በኋላ የነበረው ሁኔታ ለዚህ ምስክር ነው:: ዛሬም አንዳንዶች ወያኔ አረመኔ ነው፤ እርሱን መፈታተን አደገኛ ነው:: ዝም ብለህ አርፈህ ተቀመጥ ማለት ይቀናቸዋል:: ይህ ስሜት የሽብሩ ውጤት ነው:: ለሽብር አለመሸነፍ፤ እጅ አለመስጠት ስንል የወያኔ አረመኔነት እንዳለ ሆኖ ሕዝብ ቆርጦ ከተነሳ መለስ ዜናዊ ም ቢዳፍቅ ከወረቀት ነብርነት እንደማያልፍ ማመን ማለት ነው:: አሻፈረኝ ብሎ መሰለፍ፤ ተባብሮ መቃወም፤ በጋራ የሥራ ማቆም አድማ ማድረግ፤ ታስረው ከተሰቃዩ ሀገር ወዳዶች ፅናት ትምህርት መቅሰም፤ የታሰሩትን መጠየቅ ቤተሰቦቻቸውን በገንዘብና በሞራል እየረዱ ከጎናቸው መቆም፤ ሲረሸኑ ሕዝብ ያቸ ፋል ብለው ህያው መልዕክት አስተላልፈው ያለፉትን ግን ዛሬም ስማቸው ህያው የሆነውን ማስታወስ መራራ ትግል ለመጋተር ሞራል ይሰጣል:: መለስ ዜናዊ የሚኩራራበት ጦርም አባሎች በአብላጫው ከድህው ሕዝብ ክፍል ስለሆኑ ሰልፋቸውን ከሕዝብ እንዲያደርጉ ተገቢውና ያልተቋረጠው ቅስቀሳ ከተካሄደ ደግሞ እሰየው የምንለው ውሳኔ

ወስደው ወደ ሕዝብ ጎራ ሊመጡ ይችላሉ፡፡ በወገኖች ላይ ጠመንጃ አናወድርም-አንተኩስም ብለው ሊቃወሙ ይችላሉ፡፡ የመለስ መንጋም እርቃኑን ወጥቶ ይቀራል፡፡ ይህ ሁሉ በታሪክ የታየ ሂደትና ክስተት ቢሆንም ዋናው መፍትሄ ትግልን ማፋፋም ነው፡፡ ትግል ሲጠናከር የገዢው ክፍል ቀውስ ይበዛል፡፡ ይከፋፈላል፡፡ ይዳከማል፡፡ የሽብር ኃይሉም ይልፈሰፈሳል ይርበተበታል፡፡ በመጨረሻም ሽንፈትን ይከናነባል፡፡ ሽብር በዘለቄታው የመለስ አገዛዝ ከውድቀቱ አያድነውም፡፡ ትግላችን ይፋፋም፡፡ ጎልም እንደ ፈቺ፣ ሽብር እንደፈርጁ ነው፡፡ ስለሆነም፣ በአሁኑ ወቅት አሸባሪው መለስ ዜናዊ እንጅ ሀገር ወዳዱ የተቃዋሚ ድርጅቶች አይደሉም።